# ዴሞክራሲያ

**************************************************
* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሣን*
**************************************************

ቅጽ 33 ቁጥር 1 ጥር 2000 ዓ. ም.


## ፍትሕ እኩልነትና ዴሞክራሲን ለተጠማ ሕዝብ - ጦርነት?

### የህወሓትና የሻዕቢያ ጦርነት ሁኔታ

ምስራቃዊው የሃገራችን ክፍል ኦጋዴን ዛሬ በጦርነት እየጋዬ ነው፡፡ ሕፃን፥ ወጣት፥ አዛውንት፥ ወንድና ሴት ሳይለይ ነዋሪው በቦምብ ናዳ እየተጨፈጨፈ ይገኛል፡፡ ይህ በህወሓት አገዛዝ እየተፈጸመ ያለው ፍጅት ዓለም እየታዘበውና ጋዜጠኞችም እየዘገቡት የሚገኝ አሰቃቂ የጦርነት ወንጀል የታሪካችን አንዱ ምዕራፍ ከሆነ ሰንብቷል፡፡ አምባገነናዊው አገዛዝ ዓለም አቀፋዊ ውሎችንና ደንቦችን ጥሶ፥ እንዲሁም ድንበር ዘልሎ፥ ነጻ ሃገር የሆነችውን ሶማሊያ በመውረርና ዋና ከተማይቱን ሞቃዲሾን በሃይል በመያዝ፥ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች በዋና ከተማይቱና በሶማሊያ በረሃዎች ውስጥ እንዲረግፉ አድርጓል፡፡ ሬሳዎቻቸው በየአውራ ጎዳናዎች ላይ እየተጎተቱም ጥቃቱ ላስቆጣቸውና ለኢትዮጵያ ጥላቻ ላደረባቸው ሁሉ የቂም መወጫ ሆነዋል፡፡ ይህ አሰቃቂ ሁኔታ ለመተንበይ በሚቻል የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊቀየር ይችላል ብሎ ለማመንም እጅግ አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ የህወሓት የሶማሊያ ወረራ ያለጥርጥር ብዙ ጠላቶችን ለኢትዮጵያ አትርፏል፡፡ በሌላ በኩል ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ታጥቆ የተነሳው የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ኢትዮጵያን በጠላትነት በፈረጁ አገሮች እየተረዳና እየታጠቀ ወታደራዊ ይዞታውን እየገነባ ለመሆኑ በቅርቡ ካደረሳቸው ጥቃቶች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሶማሊያ ውስጥም የሶማሊያ የነጻነት ኃይሎች የሚባሉ ተዋጊዎች ራሳቸውን በተለያዩ መልኮች እያሰባሰቡና የጥቃት ስልቶቻቸውን እያሻሻሉ የከፋ አደጋ በማድረስ ላይ ናቸው፡፡

በምስራቅ በኩል የደረሰብን ብሔራዊ ሀፍረትና የተደቀነብን ግዙፍ አደጋ ሳያንሰንና ኤይድስ ወባና ሌሎች ቀሳፊ በሽታዎች በህዝባችን ላይ እያደረሱት ያለው እልቂት ሳያባራልን፥ ህወሓትና ሻዕቢያ ስልጣንን በጠመንጃ ከተቆጣጠሩ በኋላ ሰሜናዊውን የአገራችን ክፍል ለሶስተኛ ዙር የጦርነት እልቂት እያዘጋጁት ነው፡፡ በሁለቱ ፀረ-ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሀይሎች መካከል የሚደረጉት ጦርነቶች ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚጎዱና መወገዝ ያለባቸው ወታደራዊ ፍጅቶች እንጂ በምንም መልካቸው ለኢትዮጵያ ጥቅም የሚያግዙ ብሄራዊ ግዳጆች እንዳልሆኑ ጠንቅቆ መገንዘብ ቀዳሚ ተግባር ይሆናል፡፡

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ኤርትራና ኢትዮጵያ ሁለት የተለያዩ አገሮች ናቸው ብሎ አያምንም፥ አይቀበልም፡፡ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካልና ግዛት ስለመሆንዋ በርካታ የታሪክ ምሁራንና ዓለምአቀፋዊ ሰነዶች ካሁን ቀደም በተደጋጋሚና በበቂ መስክረዋል፤

አረጋግጠዋል። ከሁሉም በላይ የኤርትራ ኢትዮጵያዊነት የተመሰከረውና የተረጋገጠው በኤርትራ ክፍለ ሀገር ተወላጆች ደምና መስዋዕትነት ነው። ኢትዮጵያን በበጎ ዓይን ይመለከቱ ያልነበሩ የውጭ መንግስታት፥ በተለይም እንግሊዝ፥ አርጀንቲናና ፓኪስታን ፋሺስት ጣሊያን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድል ስትመታና በርሷ ቅኝ ግዛት ስር ስትማቅቅ የነበረችው ኤርትራ ወደ እናት ሃገሯ ኢትዮጵያ እንዳትመለስ አሻጥሮች ሲጎነጉኑ፥ በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግስት የረቀቀ የዲፕሎማሲያዊ ትግል ላይ ተጨምሮ፥ የኤርትራን ኢትዮጵያዊነት ያረጋገጠውና ያስከበረው የክፍለ ሀገሩ ተወላጅ አባቶቻችንና እናቶቻችን ታላቅ ተጋድሎ ነው። የዛሬዎቹ ሁለት ፀረ-ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሀይሎች፥ ህወሓትና ሻዕቢያ፥ ታሪክ ደልዘው ሰርዘውና በርዘው፥ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል እንዳልነበረች አድርገው፥ "ሃገር ነፃ ወጣ፤ መንግስት ተመሰረተ" እያሉ ሲያጨበረብሩ ቆይተው አሁን ደግሞ መልሰው ህዝብን በጦርነት ሲያፋጁና ሊያፋጁ ሲዘጋጁ ወንጀላቸውን በዝምታ መመልከት በተባባሪነት ያስወቅሳል፤ ያስጠይቃልም።

በኤርትራ የተቋቋመው ፌደራላዊ አስተዳደር ሲፈርስና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና በደርግ ዘመን ኤርትራ የጦርነት አውድማ ስትሆን፥ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የኤርትራ ችግር በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዲፈታ ታግለዋል፥ ለዚህም የደምና የህይወት ዋጋ ከፍለዋል። ይህንንም ያደረጉት በኤርትራ ሙሉ የኢትዮጵያ ግዛትነትና አካልነት በማመን፥ እንዲሁም ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር መልሶ በ1944 ዓ. ም. በፌደሬሽን የቀላቀለው የኤርትራ ክፍለ ሀገር ተወላጆች የኢትዮጵያዊነት ስሜትና ፍቅር እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ በመሆን ነው። ይህ እምነት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ዛሬም የጸና ነው - በኤርትራ ውስጥ በፍጹም የአምባገነንነት ቀንበር ስር የሚማቅቁ ወገኖቻችን የኢትዮጵያዊነት ስሜታቸውንና ፍቅራቸውን ለመግለጥና የሚፈልጉትን በሙሉ ነፃነት ለመምረጥ ዕድሉን ቢያገኙ።

እንደሚታወቀው የደርግ ፋሽስታዊ መንግስት በኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ሲወድቅ ኢትዮጵያ ሌላ ችግር ውስጥ ገባች። ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር በማበር ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ለሰላሳ ዓመታት ኢትዮጵያን ሲወጋ የነበረው ሻዕቢያ የኤርትራን ክፍለ ሀገር ተቆጣጠረ፤ ኢትዮጵያን የሚጠላው ህወሓትም የተቀረውን የኢትዮጵያ ክፍል ያዘ። ለጥቆም የሁለቱም የማጭበርበርና የክህደት ተግባር አይሎ ኤርትራ የኢትዮጵያ አይደለችም ተባለ፥ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም የኤርትራን ሌላ አገርነት እንዲያውቅ የህወሓት ማመልከቻ ቀረበለት፥ ሌላ ባንዲራ በአስመራ ተውለበለበ።

በአኳያው ትዕይንቱ በኤርትራ ክፍለ ሀገራችን ውስጥ ሲከናወንና ህዝቡ “አርነት ወይም ባርነት” ምረጥ ተብሎ በመሳሪያ አፈሙዝ ሲገደድ፥ በወቅቱ ኢትዮጵያ በጥላቻ ጭምር በሚገዛት የፖለቲካ ድርጅት (ህወሓት) ታፍና ታጣጥር ነበር እንጂ ለብሄራዊ ጥቅሟና ደህንነቷ የቆመ ብሄራዊ መንግስት አልነበራትም። በወቅቱ ከነበሩት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የአንድነት ኃይል ድርጅቶች፥ በተለይም ኢሕአፓ አባል በነበረበት በኢዴኃቅ ውስጥ ተጠቃልለው የነበሩት፥ የኤርትራውን ተውኔት በመቃወም ከበርካታ የብዙኃን ማኅበራትና ከታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች፥ እንዲሁም ከሃይማኖት መሪዎችና ምሁራን ጋር በመሆን መራር ተቃውሟቸውን ለተባበሩት መንግስታትና ለአፍሪቃ አንድነት ድርጅት አሳውቀዋል። ኢትዮጵያ በወቅቱ በተወሰኑት ውሳኔዎችና በተፈረሙት ማናቸውም ውሎች ለወደፊት ልትገዛ እንደማትችልም አስጠንቅቀዋል። ለዚህም ነው አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የአንድነት ኃይሎች፥ ኢሕአፓን ጨምሮ፥ ዛሬም ኤርትራን እንደሌላ አገር ያልተቀበሉትና የማይቀበሉት። ስለዚህ፥ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በኢትዮጵያና በአካሏ በኤርትራ መካከል የወሰን ግጭት ነበር ወይም አለ ብሎ አያምንም። ካሁን ቀደም በሻዕቢያና በህወሓት አምባገነናዊ ሀይሎች የተደረገውና በመቶ ሺህ ለሚቆጠር ህይወት መጥፋት መንስዔ የሆነው ጦርነት ህገ-ወጥ ነበር ፥ ታሪክ ይቅር የማይለው እጅግ ከፍተኛ ወንጀልም ነው። ጦርነቱ ከእንግዲህም ሊደገም የማይገባውና የኢትዮጵያ ህዝብ፥ እንዲሁም

ወንድምና እህት የሆኑት ኤርትራ ውስጥ ያሉት ወገኖቹ ጭምር፥ አጥብቀው ሊቃወሙትና ሊያቆሙት የሚገባ ፍጅት ነው፡፡

ሌላው በግልፅ ሊታወቅ የሚገባ ጉዳይ የጦርነቱ መንስዔ ወይም ምክንያት ነው፡፡ ባድመ በማን ግዛት ስር መሆን እንዳለባት ለማስረገጥ ነው የሚለው የሁለቱም ታሪክ በራዦች ጩኸት ሕዝብን ለማደናገር የተቀመረ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ መሆኑ ከተረጋገጠ ቆይቷል፡፡ ትናንት ከትናንት በስቲያ "ኤርትራ የምትባል አገር አለችና ነጻነቷን ቶሎ እወቁልኝ" ብሎ የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪቃ አንድነት ድርጅቶችን ወጥሮ ይዞ ኢትዮጵያን ያለምንም የባህር መውጫ በር ታፍና እንድትቀር ያደረገው ህወሓት እውን ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር ተቆጭቶ በጠላቶቿ ላይ ሊዘምት ነውን? እንዲህም ብሎ ለማመን ግብሩና ምክሩ ዱባና ቅል ናቸውና ከቶውንም ተዓማኒነት የለውም፡፡ ሻዕቢያም ቢሆን በትብብር በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ፈጅቶ ከወታደራዊው መንግስት እጅ ፈልቅቆ ያሁኑን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱን ትውልድ ሳይቀር እጅጉን በሚጎዳ መልኩ የኤርትራን ክፍለ ሃገር ያስረከበውን ህወሓት በቁራሽ መሬት ወሰደብኝ ሊጣላው ነው? የዘመናት የግንጠላ ቀንደኛ ተባባሪውን ከመቅፅበት ይከዳዋል ብሎ ለመቀበል ከቶውንም አይቻልም፡፡ የጦርነታቸው ዋነኛ መነሻ ምክንያት  ከተጠቀሱት ነጥቦች ሁሉ እጅግ የራቀ ነው፡፡ "ሌባ ሲካፈል እንጂ ሲሰርቅ አይጣላም"  እንዲሉ የዛሬዎቹ ጣምራ አምባገነኖች፥ ሻዕቢያና ህወሓት፥ የተናከሱበት ዋናው ምክንያት የወደፊቱን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ህይወትና የኤኮኖሚ ምንጮቿን ማን ይቆጣጠረዋል በሚለው ቁልፍ ጥያቄ ላይ ነው፡፡

ምንም እንኳን ህወሓት የሚቆጣጠራት ኢትዮጵያ ሻዕቢያ ከያዛት ኤርትራ በቆዳ ሽፋንና በህዝብ ብዛት ይሁን በኤኮኖሚ ሀብት የምትበልጥና የሁለቱ አምባገነኖች የሀይል ሚዛን ሲሰላ ወደ ህወሓት የሚያመዝን ቢመስልም ሻዕቢያ ህወሓትን ኮትኩቶና መግቦ ያሳደገው በመሆኑ ብቻ እንዳዘዘውና እንደተቆጣጠረው የሚኖር ይመስለው ነበር፡፡ እንዲያውም ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሰቀመጠው ወኪል መንግስት ሳይቆጥረውም አልቀረም፡፡ ለዚህም ነው “ኤርትራ የግላችን፥ ኢትዮጵያ የጋራችን” እያለ ሻቢያ ለተወሰነ ወቅትም ቢሆን በህወሓት ፈቃድ የኢትዮጵያን ሀብት ሲበዘብዝ የቆየው፡፡ ሻዕቢያ ሁልጊዜ ኢትዮጵያን በመቆጣጠር ኤርትራን "የአፍሪቃ ሲንጋፖር"  ለማድረግ እችላለሁ ብሎም አምኖ ነበር - የዛሬን አያድርገውና፡፡ ለአብነት፥ በአንድ ወቅት ቡናን በማፍራት የማትታወቀው ኤርትራ ከዓለም አምስተኛዋ የቡና አምራችና ላኪ አገር ተብላ እንደተቆጠረች መጥቀሱ ይበቃል፡፡

ሻዕቢያ በምንም የኤኮኖሚ መመዘኛ ሊደገፍ የማይችለውን ናቅፋ የተባለውን  ገንዘብ አትሞ ከኢትዮጵያ ብር ጋር መሳ ለመሳ ሊለወጥ እንዲችልና ማንኛውም ግዢ ኢትዮጵያ ውስጥ በናቅፋ እንዲከፈል ሲወስን በቀጥታ የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ ለመቆጣጠር እችላለሁ ከሚል ግምት ተነስቶ ነው፡፡ ዛሬ፥ ወርቅ የገንዘብ መመዘኛነቱ ከቆመ በኋላ፥ በነጻ የገንዘብ ልውውጥ ገበያ ውስጥ የአንድ ሃገር ገንዘብ ዋጋ የሚወሰነው በዚያ ሃገር የኤኮኖሚ ጥንካሬ፥ የእድገት ደረጃና ፍጥነት ነው፡፡ ናቅፋ ከነዚህ የኤኮኖሚ መመዘኛ ነጥቦች አኳያ ሲታይ ለታለመው የሻዕቢያ ፍላጎት ብቃት የለውም፡፡ ህወሓትም ለብዙ ሺህ ዓመታት በታሪክና በባህል ተሳስሮ የኖረን ሕዝብ እንደዋዛ አሳልፎ ሲሰጥና ሃገርን ያለባሕር በር ሲያስቀር ቅንጣት ታሕል ሳይቆረቁረው ሻዕቢያ ፈርጠም ሲልበትና በግል ጥቅሙ ሲመጣበት አሻፈረኝ አለ፡፡ በህወሓት እምቢተኝነትም አሳዳጊው ሻዕቢያ እጅጉን ተቆጣ፡፡ ስለዚህ ህወሓትን ለመቅጣት ወሰነ፡፡ ጦርነት ተጀመረ፥ ከመቶ ሺህ በላይ ሰራዊት ከሁለቱም ወገን አለቀ፡፡ ከሶስት መቶ ሺህ በላይ ህዝብም ተፈናቀለ፡፡

ህወሓት ያሰለፈው ጦር በከባድ መስዋዕትነት በሻዕቢያ በኩል በተሰለፈው ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል፡፡ ከምን ጊዜውም በበለጠ የሻዕቢያ ጦር ሞራል እንዲወድቅና ጥንካሬው እንደገና እንዲፈተሽ አድርጓል፡፡ በሀሰት የተገነባው የሻዕቢያ ብሄራዊ ስሜትም ክፉኛ ተመቷል፡፡ ነገር ግን፥ ያ ሁሉ መስዋዕትነት ተከፍሎ፥ ያ ሁሉ ንብረት ወድሞ፥ ያ ሁሉ ገንዘብ ባክኖ፥ ያ ሁሉ ህዝብ ተፈናቅሎ፥ በህወሓት ሲደረደር የነበረው የጦርነቱ ዋና

ምክንያት ከመቅጽበት በንኖና ተኖ የተሰለፈው ጦር ያሰበበት ሳይደርስ፥ የፈለገውን ወታደራዊ ድል ሳይቀዳጅ፥ በአቶ መለስ ዜናዊ ብቸኛ ቀጭን ትዕዛዝ ጦርነቱ ተጨናገፈ። የሻቢያ መንግስት ተረፈ፥ ኢትዮጵያ አሁንም ያለ ባህር በርና ወደብ እንደታፈነች ቀረች። በተገኘው ወታደራዊ ድል በመታገዝ ኢትዮጵያ በቀድሞ ውሳኔዎችና ውሎች ያጣቻቸውንና የተጎዳችባቸውን በሙሉ መልሶ ከማስገኘት ይልቅ የህወሓት አገዛዝ ኢትዮጵያን የማይጠቅሙ ዶሴዎች ሰብስቦ ወደ አልጄርስ በረረ፥ በጦር ሜዳም አገኘሁ የሚለውንም ድል ለሻዕቢያ አስረክቦ ተመለሰ። ከባድ ክህደት፥ ታሪክም ትውልድም ይቅር የማይሉት ጥፋት።

ከአልጀርስ መልስ፥ ህወሓት የፈረመውን የክህደት ውሳኔ ተከትሎ፥ ሄግ (ኔዘርላንድ) ላይ ጉዳዩን የሚመለከትና ውሳኔ የሚሰጥ የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ተሰየመ። የህወሓት አገዛዝ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ማስጠበቅ ዓላማው አይደለምና የሻዕቢያን ክብር ሊነኩ የሚችሉ ነገሮች ላለመፍቀድ ሲል በተሰየመው የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ላይ ኢትዮጵያ በአግባቡ እንዳትወከልና በጉዳዩ ላይ አጥብቃ ለመከራከር እንዳትችል አደረገ፤ ታማኝነታቸውና አገልጋይነታቸው ለማን እንደሆነ በውል የማይታወቁ የውጭ አገር ጠበቆችን ቀጠረ። ቀደም ባሉ ዘመናት የነበሩ የኢትዮጵያ መንግስታት፥ በተለይም አጼ ምንልክ፥ ያልተቀበሏቸውንና በ1928ቱ የጣሊያን ወረራ ምክንያት የተሰረዙትን የ1894 ዓ. ም. እና የ1901 ዓ. ም. ውሎችን እንደመረጃና እንደመከራከሪያ ሰነድ አቀረበ። በመሆኑም በተባበሩት መንግሰታት ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የተሰየመው የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን በጣም አጠራጣሪና አጠያያቂ በሆነ መንገድ ለሻዕቢያ መንግሰት የሚያደላ የድንበር ውሳኔ አስተላለፈ። ውሳኔው እንደተላለፈ የህወሓት አገዛዝ በአስገራሚ መልኩ አሸነፍኩ ብሎ አቅራራ፥ ደሰኮረ። ወዲያው ደግሞ፥ ያለምንም ሀፍረት፥ አሸነፍኩ ብሎ በተናገረበት አፉ ዞር ብሎ የኮሚሽኑ ፍርድ አልተሰማማኝም አለ። የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ ይግባኝ የማይጠየቅበት መሆኑን ቀደም ሲልም እያወቀ ተስማምቶና ፈርሞ ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ ግን በሚገርምና በሚያደናግር መልኩ ይግባኝ እጠይቃለሁ አለ። ኮሚሽኑ ለይግባኝ አልቀመጥም ሲል ሻዕቢያም እንደገና አልዳኝም አለ። የሚያስገርሙ መለዋወጦች ዋነኛ ባሕሪይው የሆነው የህወሓት መንግሰት ቁንጮ አቶ መለስ ዜናዊ እንደልማዱ እንደገና በቅፅበት ሃሳቡን ቀይሮ "የኮሚሽኑን ውሳኔ በመሰረተ ሀሳብ ደረጃ እንቀበላለን፥ ነገር ግን በዝርዝር ሁኔታዎች ላይ ከሻዕቢያ ጋር ለመነጋገርና ለመደራደር እንፈልጋለን" አለ። ይህ የማይጨበጥ የህወሓት የፖለቲካ ማደናገሪያ ተብሎ ቢታለፍም የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ጉዳዩን አስመልክቶ ዛሬ ያለውን ቁርጠኛ አቋም ለማወቅ አስቸግሯል። የኮሚሽኑን ውሳኔ ተቀብሏል ወይስ አልተቀበለም? ከተቀበለስ፥ የድንበር ማካለሉን ተግባር ለምን አልጀመረም? የኮሚሽኑን ውሳኔ ላለመቀበል ወስኛለሁ ካለ ምን ሌላ አማራጭ አቅርቧል? እንዴት አድርጎ የድንበሩን ውጥረትና ግጭት ሊፈታው አስቧል? ውጥረቱስ እስከመቼ ይቀጥላል? ከኢትዮጵያ ህዝብስ ምን ይጠበቃል? ለሚሉ ጥያቄዎች ህወሓት ዛሬም በቂ ምላሽ የለውም። ሻዕቢያ ግን የፖለቲካ ህይወቱ የተንጠለጠለችው በዚህ የድንበር ማከላል ውሳኔና መፈጸም ላይ ይመስላል።

የህወሓት አገዛዝ የተገኘውን ወታደራዊ ድል ለማስነጠቅ ወደ አልጀርስ ሲጓዝና በተባበሩት መንግሰታት ዓለም አቀፋዊ ፍርድ ቤት የተሰየመው የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን ሲሰየም በአገር ቤትና በውጭ አገሮች ያሉ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች፥ የብዙሀን ማኅበራት፥ የሀይማኖት መሪዎች፥ የአገር ሽማግሌዎችና ምሁራን ተቃውሟቸውንና ቅሬታቸውን በሰላማዊ ሰልፎች፥ በፅሁፍና በአቤቱታ መልክ ለተባበሩት መንግሰታት ፅህፈት ቤትና ለዓለም አቀፋዊው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፥ አሰምተዋል። ዳሩ ግን፥ አትዮጵያዊ ተቋማቱ፥ ስብስቦቹና ግለሰቦቹ በተባበሩት መንግሰታትና አካሉ በሆነው ዓለም አቀፋዊ ፍርድ ቤት ውስጥ ምንም ህጋዊ ውክልናና መቀመጫ ስለሌላቸው ሊደመጡ አልቻሉም፥ ጉዳያቸው አልታየላቸውም። ሆኖም ግን፥ ተቃውሟቸውና ጥረታቸው በሁሉም ዓለም አቀፋዊ ተቋሞች ማኅደር ላይ ለታሪክ ተመዝግቦላቸዋል።

ይህ የህወሓትና የሻዕቢያ የጦርነት ሁኔታ ዛሬ ምን ላይ ይገኛል? እኛስ ምንስ ማድረግ ይኖርብናል? የህወሓት አገዛዝ "ኤርትራን ለመውጋት አንፈልግም" እያለ ጠዋት ማታ ቢምል ቢገዘትም፥ በሰሜናዊው የአገራችን ክፍል ጦርነት ሊነሳ እንደሚችል የሚያመለክቱ በርካታ ሁኔታዎች አሉ። የአገራችንና የህዝባችን የኤኮኖሚ አቅም ሊሸከማቸው የማይችላቸው ወታደራዊ ክምችቶች በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል በሻዕቢያም በህወሓትም በኩል እንደቀጠሉ ናቸው። የተባበሩት መንግስታትም ስጋቱን እየገለጠና ከጦርነት እንዲታቀቡ ሁለቱንም ክፍሎች እየተማጸነ ይገኛል። ኢትዮጵያም ዛሬ ከሰሀራ በረሀ በታች ካሉት የአፍሪቃ አገሮች ውስጥ በጦር መሳሪያ ግዢ አንደኛ መሆኗ በዜና አውታሮች ይነገራል። ሻዕቢያም ህወሓትም የነርሱን የውክልና ጦርነት ሊያካሄዱ የሚችሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን እየመሰረቱ፥ እያሰለጠኑ፥ እያስታጠቁና ድንበር አሳልፈው አንዳንድ የደፈጣ ውጊያዎችን እያስጀመሩ ናቸው። ሻዕቢያ ውስጣዊ መረጋጋትንና ተቀባይነትን ለማግኘት ሲል ብቻ ወደ ጦርነቱ ሊገፋ ይችላል። ምንም እንኳን የህወሓትን አስተሳሰብና አካሄድ መገመትና መተንበይ አስቸጋሪ ቢሆንም፥ ውስጣዊ ውጥረት እያየለበትና እየሰጋው ሲመጣ፥ የኢትዮጵያውያንን ብሄራዊ ስሜት አሳምሮ ያውቃልና ሊነሱበት የሚችሉ ውስጣዊ ተቃውሞዎችን ለማዳፈን ሲል ጦርነት ሊጀምር ይችላል። ጦርነቱ ከተጀመረ ጠቅላላ የህዝብና የንብረት መውደም ይከተላል። ስለዚህ፥ የኢትዮጵያ ህዝብ በምስራቃዊው ክፍላችንና ሶማሊያ ውስጥ የሚካሄደውን ዓላማ ቢስና ማለቂያ የሌለውን ጦርነት አጥብቆ እንደሚቃወመው ሁሉ፥ በሰሜናዊው ክፍላችን ሊከሰት የሚችለውን ጦርነት በቁርጠኝነትና ያለምንም ማወላወል አጥብቆ መቃወም ይኖርበታል።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ ኢትዮጵያና ኤርትራ አንድ አገር እንጂ ሁለት የተለያዩ አገሮች አይደሉም። ስለዚህ የድንበር ግጭት ሊኖር አይችልም። ለሃምሳ ዓመታት የሃሰት ድንበር በጣሊያን ቅኝ ገዥዎች በሚጣልበት ጊዜ እንኳን ህዝቡ በድንበር ሳይወሰን እንደ አንድ ኅብረተሰብ ደስታና ሀዘን እየተጋራ እየተጋባና እየተዋለደ አብሮ ኖሯል። በ1985 ዓ. ም. ኤርትራ ውስጥ ተካሄደ በተባለው ሬፈረንደም ኤርትራ ነጻ አገር ሆናለች የሚል ክርክር ቢነሳ እንኳን ትክክል እንዳልነበረ ብዙ ግድፈቶችን ለመዘርዘር ይቻላል። ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ፤ (1ኛ) የሬፈረንደም ጉዳይ ሲነሳ፥ ሌላኛውን የኢትዮጵያ ክፍል ትተን፥ ኤርትራ ውስጥ ለሬፈረንደሙ በቂ ዝግጅት እንዳልነበረ ለማሳዬት ይቻላል። ሬፈረንደም ማለት የተለያዩ አማራጭ ሀሳቦች ቀርበው ህዝብ ተነጋግሮና ተከራክሮባቸው ሙሉ ግንዛቤ አግኝቶ ጥቅሙንና ጉዳቱን ለይቶ ልባዊ ፍላጎቱን ያለምንም ተጽዕኖ ለመምረጥና ለማሳወቅ መቻል ማለት ነው። ይህ ኤርትራ ውስጥ አልተደረገም። በማስፈራራትና በማስገደድ ለአካባቢው ነዋሪ “ባርነት ወይም አርነት” የሚል ምርጫ ብቻ ቀርቦለት ህዝቡ ተገድዶ የመረጠበት ሬፈረንደም ነው። ይህንን ሬፈረንደም ያካሄዱትና እውቅናም የሰጡት መንግስታት በሙሉ፥ በተለይም የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የአፍሪቃ እንድነት ድርጅት ታላቅ ስህተት ፈጽመዋል፥ ኢትዮጵያን በድለዋል። (2ኛ) ጣሊያን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድል ስትመታና ኤርትራ ወደ እናት አገሯ በፌደሬሽን እንደትመለስ ሲወሰን የቀረቡት ህጋዊ፥ ማህበራዊ፥ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ምክንያቶች ከቁም ነገር ሳይቆጠሩ ኢትዮጵያ ደክማ ስለተገኘችና ለአገሪቱም ለህዝቧም ደንታ በሌለው ድርጅት፥ ማለትም በህወሓት፥ በመገዛቷ ብቻ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተቆርሳ እንድትሄድ መደረጉ ከፍተኛ ስህተትና ለወደፊቱም ብዙ ችግሮችን የሚያስከትል ጥፋት ነው። (3ኛ) ስለኢትዮጵያ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ የባህር መውጫና መግቢያ በር ጉዳይ የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይመክርበትና ሳይደመጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ህዝብ የያዘች ታሪካዊ አገር በኤኮኖሚ ድህነት እንድትታነቅና ብሄራዊ ደህንነትዋ ለዘለዓለሙ አደጋ ላይ እንዲወድቅ ሲደረግ ሌላ የረጅም ጊዜ ችግርን መጋበዝ ነው። (4ኛ) ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትቆረስ የንብረትና የዕዳ ክፍፍል እንዴት መሆን እንዳለበት ሳይታወቅና ሳይተመን፥ የመልክአ ምድሯ አቀማመጥና ካርታዋ፥ ማለትም ወሰኗ፥ ምን እንደሚመስልና በድንበር ላይ ያሉ ኗሪዎች ከወዴት መሆን እንደሚገባቸው ሳይወሰን በዘፈቀደ በተሳለ ካርታ አገርን መመስረት ግዴለሽነት ነው። በነዚህና ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች ኢትዮጵያ ኤርትራን እንደ አንድ ሌላ ነጻ አገር ልትመለከት አትችልም።

ስለዚህ÷ አበክሮ ለማሳወቅ ያህል÷ ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር የድንበር ግጭት የላትም÷ ድንበር ለማስከበር የምታደርገውም ጦርነት የለም÷ የችግሩ ምንጭ ሌላ ነው::

በህወሓትና በሻዕቢያ እየተደገሰ ያለውን ጦርነት መቃወም የግድ የሚያደርገው ሌላኛው ትልቁ ምክንያት ያለፈው ተመክሮአችን ነው:: ከላይ እንደተገለጠው ህወሓት ለኢትዮጵያ የሚጨነቅ ቢሆን ኖሮ ከፍተኛ ወታደራዊ ድል በ1992ቱ ጦርነት ተገኝቶ ነበር:: ኢትዮጵያ ኤርትራን አስመልክቶ ልታደርግ የምትፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ ያለምንም ችግር ልታደርግ ትችል ነበር:: ሌላ ዙር ጦርነት ውስጥ ሳትገባ ማለት ነው:: ነገር ግን ከሃዲው የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ዋና ጭንቀቱ የሻዕቢያን መንግስት ሕይወት ማትረፍ እንጂ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ማስከበር ስላልነበረ ጦርነቱን አክሽፎ የተገኘውን ወታደራዊ ድል መና አስቀርቶታል:: ዛሬ በምኑ ታምኖ ነው ዓላማው በግልጽ ላልታወቀ የህወሓት ስውር ደባ የኢትዮጵያውያን ደም በከንቱ የሚፈሰው? ከሀዲ መንግስት ብሄራዊ ጦር አይመራም÷ ብሄራዊ ጦርነትም ሊያካሄድ አይችልም:: ስለዚህ÷ ኢትዮጵያውያን በህወሓት የሚጫሩ ጦርነቶችን መቃወም ይኖርባቸዋል÷ በተመሳሳይ መልኩ በኤርትራ ውስጥ ያሉት ወገኖቻችንም በሻዕቢያ የሚጫሩ ጦርነቶችን መቃወም ይገባቸዋል::

የህወሓት አገዛዝ ጦርነት ቀፍቃፊ አገዛዝ ነው:: የእስካሁን ታሪኩ እንደሚያሳየው የገባባቸው ጦርነቶች ሁሉ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት ያስጠበቁ አይደሉም:: አገዛዙ ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር ደንታ የሌለው ለራሱ ቡድናዊ ጥቅምና ለባዕዳን ጌቶቹ ብቻ ያደረ ጥገኛ አገዛዝ ነው:: አገሪቱን በዘር ከፋፍሎ ለእርሱ ባልሆነ ጊዜ በትኖ ለመጥፋት የተዘጋጀ÷ ኤርትራን ያስገነጠለና አገራችንን ያለ ባህር መውጫ በር ያስቀረ÷ የኢትዮጵያን ግዛት ለሱዳን አሳልፎ የሰጠና የአገሪቱን ተፈጥሮአዊ ሀብቶች እየበዘበዘና እያስበዘበዘ የሚገኝ ወንጀለኛ አገዛዝ ነው:: ቀደም ሲል እንደጠቀስነው በጌቶቹ ትዕዛዝ ሶማሊያ ውስጥ በድንበር ዘለልተኝነትና በጣልቃ ገብነት የሚያደርገው ጦርነት ለወደፊቱ ኢትዮጵያን እያመሰ የሚኖር ታላቅ ችግር እንጂ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት የሚያበረክተው አንዳች ፋይዳ አይኖረውም:: በኦጋዴን ውስጥ እየፈጸመ ያለው ኢሰብዓዊ ጭፍጨፋ የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነትና ህብረት ለዘለዓለሙ የሚያሻክርና የሚያናጋ ነው:: ቀደም ሲልም በአዋሳ በወላይታ በነቀምት በአርሲ በጎንደር በጂማ በጋምቤላና ሌሎችም አካባቢዎች የፈጸመው ገደብ የለሽና አሰቃቂ ፍጅት ለረጅም ጊዜ ሊፋቅ የማይችል የታሪካችን ጠባሳ ነው:: አሁንም ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ በኦሮሞ ህዝብ ላይ በየዕለቱ እያካሄደ ያለው እስራት ግድያና በደል ለኢትዮጵያ ህዝብ የተደላደለና የተረጋጋ ኑሮ መሰረታዊ ጠንቅ ነው:: ኢትዮጵያ በሁሉም ማዕዘንና አቅጣጫ በጦርነት ተወጥራ መኖርን አትፈቅድም:: ጦርነትን ተከትለው የሚከሰቱ የኤኮኖሚ ድቀቶችና የማኅበራዊ ኑሮ መናጋቶች ኢትዮጵያ ከምትችለው በላይ ይሆንባታል:: የህወሓት አገዛዝ ደግሞ ከጦርነት ውጭ በተረጋጋችና በሰላማዊት ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር አይፈለግም÷ አይችልምም:: ሰላማዊና የተረጋጋች ኢትዮጵያ መኖር ለሰብዓዊና ለዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበርና ለመንግስት ተጠያቂነት የሚረዱ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያግዛል:: ይህ ሁኔታ ግን ከህወሓት ተፈጥሮና ፍላጎት ጋር ክፉኛ ይጋጫል:: ህወሓት ህዝቡንና አገሪቱን በሙሉ ጦርነትና የጦርነት ሁኔታ ውስጥ እያመሰ ለመቆዬትና ጭቆናውንና ብዝበዛውን ለመቀጠል ይፈልጋል:: የጠነከረና የተባበረ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት እስከሌለ ድረስ ይህ የህወሓት ፍላጎትና አገዛዝ ይቀጥላል:: ይህንን አስከፊ ሁኔታ ለመቀየር የሚቻለው በብሩህ ራዕይና በተጨባጭ የሚከሰቱትን አገራዊ አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ የተደራጀና የተባበረ ጠንካራ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅት ሲኖርና የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ የትግሉ ዋነኛ ባለቤትነቱን በተግባር ሲያረጋግጥ ብቻ ነው::

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!
ኢሕአፓ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያቸንፋል!!!